ዜና
አመዝኮ





# አመዝኮ በእሳተ ገሞራ ፍንዳታ እና በመሬት መንቀጥቀጥ አደጋ ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖች የምግብና የቁሳቁስ ዕርዳታ አጓጓዞ ተከፋፈለ

በአፋር ብሔራዊ ክልል በቴሩ ወረዳ መስከረም ወር አጋማሽ በደረሰው የመሬት መንቀጥቀጥና እሳተ ገሞራ ፍንዳታ ሳቢያ ከአካባቢያቸው ለተፈናቀሉ ወገኖቻችን አስፈላጊው የምግብና የቁሳቁስ ዕርዳታ ተጓጓዞ ተከፋፈለ ፣ የውኃ እጥረቱንም ለማቃለል አንድ የውኃ ቦቴ ወደ አካባቢው ተልኳል።



በመስከረም ወር አጋማሽ በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በቴሩ ወረዳ በደረሰው የመሬት መንቀጥቀጥና የእሳተ ገሞራ ፍንዳታ ሳቢያ የደረሰውን ጉዳትና የሚያስፈልገውን ድጋፍ እንዲያጠና ከፌዴራል አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን የተላከው ፈጣን የአደጋ ጥናት ቡድን ከቦታው መስከረም 24 ቀን 1998 በላከው ሪፖርት መሠረት በወረዳው ቦያና እና ደባዎ በተባሉ ቀበሌዎች ተፈናቅለው ከቴሩ 20 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ደባቦ በተባለው ቦታ ላይ ለሰፈሩ 6ሺህ 384 ተጎጂ ወገኖች 1 ሺህ 215 ኩንታል የምግብ ዕርዳታ ፣ መጠናቸው 4 ሜትር በ50 እና 30.5 ሜትር በ3 ሜትር የሆኑ 119 ጥቅል ለመጠለያነት የሚያገለግሉ ኘላስቲክ ሽቶች ፣ 18 ሺህ 234 ልዩ ልዩ መሠረታዊ የቤት ውስጥ ቁሳቁሶች እና 1ሺህ 280 የህፃናት ብርድ ልብስ ከፌዴራል አመዝኮ ተጓጉዞ ተከፋፍሏል። በአደጋው ነባር የውኃ ኩሬዎች በመውደማቸው ሳቢያ የተከሰተውን የውኃ እጥረት ለማቃለልም 15 ሺህ ሊትር ውኃ የመያዝ አቅም ያለው ተሽከርካሪ ቦቴ ወደ ሥፍራው ተልኳል።

ለአደጋው ተጎጂዎች ከተመደበው የምግብ ዕርዳታ ውስጥ 9 መቶ ኩንታል እህል ፣ 82 ነጥብ 9 ኩንታል ኃይል ሰጪ ብስኩት ፣ 101 ኩንታል አልሚ ምግብ ፣ 32 ኩንታል ዘይት ፣ 1 መቶ ኩንታል ጥራጥሬ መሆኑ ታውቋል።

ከቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶችም 1 ሺህ 200 ብረት ድስት ፣ 1 ሺህ 280 ጆግ፣ 1 ሺህ 280 ባለ 20 ሊትር ጀሪካን ፣ 426 የሻይ ማንቆርቆሪያ፣ 6 ሺህ 384 ኘላስቲክ ሣህን ፣ 6 ሺህ 384 ኘላስቲክ ኩባያ መሆኑም ታውቋል።

## በዚህ እትም ውስጥ

ከ3.7 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የምግብ እህል በብድር ተሰጠ
ገጽ 2

ብሔራዊ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ፈንድ ከ5 ሚሊዮን ብር በላይ የገንዘብ ድጋፍ አገኘ
ገጽ 2

በብር 101.7 ሚሊዮን እህልና ቁሳቁስ ከአገር ውስጥ ግዥ ተከናውኗል
ገጽ 3

በ10.5 ሚሊዮን ብር የገንዘብ ድጋፍ የ13 የ ዲዮ መገናኛዎችና 40 የእርዳታ እህል ማከማቻ መጋዘኖች ግንባታ በመከናወን ላይ ይገኛል
ገጽ 3

በአፋርና በደቡብ ክልሎች በጎርፍ አደጋ ለተጎዱ ወገኖች 3 ሺ 700 ኩንታል በላይ የምግብ ዕርዳታ ተላከ
ጽ 4

ከ431 ሺ ኩንታል በላይ የምግብ ዕርዳታ ለክልሎች ተመደበ
ገጽ 4

የላቀ አስተዋፅኦ ያበረከቱ የጥበቃ ሰራተኞች ተሸለሙ
ገጽ 5

በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ
ስልክ. 529259
529262
ጠ.ሳ.ቁ 5686
ድረገጽ፣www.dppc.gov.et

ዜና አመዝኮ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽንና ተባባሪዎቹን የሚያካሂዷቸውን የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት እንቅስቃሴዎችንና ሌሎች ተጎዳኝ ተግባራትን የሚዘግብ ወርሃዊ ልሳን ነው

# ከ3.7 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የምግብ እህል በብድር ተሰጠ

የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳዳር እ.ኤ.አ ከጥር እስከ ጥቅምት 3 ቀን 2005 ባለው ጊዜ ውስጥ 3 ሚሊዮን 790 ሺህ 438 ኩንታል እህል ለአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን ፣ መንግሥታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች እና ለዓለም ምግብ ኘሮግራም በብድር መስጠቱ ታወቀ።

ከዚሁ ብድር ውስጥ አመዝኮ 2 ሚሊዮን 937 ሺህ 400 ኩንታል ፣ መያዶች 690 ሺህ 938 ኩንታል ፣ የዓለም ምግብ ኘሮግራም 162 ሺህ 100 ኩንታል ተበድረው ለተለያዩ የዕርዳታ ሥራዎች አገልግሎት አውለውታል።

በተመሳሳይ ሁኔታ እ.ኤ.አ ከ2005 በፊትና በዚሁ ዓመት ውስጥ ከክምችቱ በተለያዩ የረድኤት ድርጅቶች ዋስትና በብድር ከወጣው እህል አመዝኮ 3 ሚሊዮን 373 ሺህ 359 ኩንታል ፣ መያዶች 906 ሺህ 470 ኩንታል ፣ የዓለም ምግብ ኘሮግራም 103 ሺህ 625 ኩንታል በድምሩ 4 ሚሊዮን 383 ሺህ 454 ኩንታል እህል ተመላሽ አድርገዋል።

እ.ኤ.አ እስከ ጥቅምት 3 ቀን 2005 አስተዳደሩ እጅ የሚገኘው የእህል ክምችት መጠን 2 ሚሊዮን 779 ሺህ 16 ሲሆን ፣ ተጨማሪ 567 ሺህ ኩንታል እህል ደግሞ ለብድር አገልግሎት ሊውል በሂደት ላይ ይገኛል። በአሁኑ ሰዓት ወደ ክምችቱ ተመላሽ መሆን የሚገባው እህል 704 ሺህ 32 ኩንታል እንደሆነም ከምግብ ክምችት አስተዳዳር የደረሰን መረጃ ያስረዳል።

የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳዳር እስከ ጥቅምት 3 ቀን 2005 አስተዳደሩ እጅ የሚገኘው የእህል ክምችት መጠን 2 ሚሊዮን 779 ሺህ 16 ሲሆን ፣ ተጨማሪ 567 ሺህ ኩንታል እህል ደግሞ ለብድር አገልግሎት ሊውል በሂደት ላይ ይገኛል።




# ብሔራዊ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ፈንድ ከ5 ሚሊዮን ብር በላይ የገንዘብ ድጋፍ አገኘ

በአደጋ ወቅት የሰውንና የእንስሳትን ሕይወት ከአደጋ ለመከላከልና የልማት ሥራዎችን ለማከናወን እንዲቻል የፈንዱን አቅም ለማጎልበት በ1997 በጀት ዓመት በተከናወነው ሥራ 5 ሚሊዮን 18 ሺ 113 ብር ሊሰበሰብ ችሏል። ከዚሁ ገንዘብ ውስጥ 3 ሚሊዮን 584 ሺ 226 ብር መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ተሽከርካሪዎች ሽያጭና ከግምጃ ቤት ጨረታ የተገኘ ነው።

ክስተት

ከዚህም በተጨማሪ የፈንዱን አቅም ለማሳደግ መንግሥት ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ ሲንቀሳቀስ የቆየ ሲሆን በበጀት ዓመቱ 1 ሚሊዮን 433 ሺ 887 ብር ድጋፍ ማድረጉ ታውቋል:: በ1996 በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ 111 ሚሊዮን 279 ሺ 342 ብር የነበረው የፈንዱ አቅም በያዝነው በጀት ዓመት ላይ 116 ሚሊዮን 279 ሺ 468 ብር ሊደርስ ችሏል::

## በብር 101.7 ሚሊዮን እህልና ቁሳቁስ ከአገር ውስጥ ግዥ ተከናውኗል

በ1997 በጀት ዓመት ውስጥ ለምግብ እጥረት ተጋልጠው ዕርዳታ ያስፈልጋቸዋል ለተባሉ ተረጂዎች 62 ሺ 943 ሜትሪክ ቶን እህልና አልሚ ምግብ በብር 101 ሚሊዮን 568 ሺ 695 ፣ ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች ማለትም 51 ሺ 14 የኘላስቲክ ኩባያና 33 ሺ 962 የኘላስቲክ ሳህኖች በብር 169 ሺ 134 ወጪ ከአገር ውስጥ ተገዝቶ ለተጎጂ ወገኖች ተከፋፍሏል::

በበጀት ዓመቱ ከማዕከላዊ መጋዘኖች ወደ ክልሎች በብር 148 ሚሊዮን 707 ሺ 660 የትራንስፖርት ወጪ 520 ሺ 917 ሜትሪክ ቶን እህል፣ 2 ሺ 462 ካርቶን ዘይት፣ 2 ሺ 69 ጥቅል ኘላስቲክ ሺትና በቁጥር 65 ሺ 338 የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶች ተጓጉዘዋል::

በኮሚሽኑ መጋዘን ውስጥ የሚገኘውን እህል በጥራት ለመያዝ በተደረገው እንቅስቃሴ 31 ሺ 719 ሜትሪክ ቶን እህል በብር 147 ሺ 600 ወጪ ጥራቱና ደህንነቱ ተጠብቆ ለተገቢው አገልግሎት እንዲውል ተደርጓል::

## በ8.5 ሚሊዮን ብር የገንዘብ ድጋፍ የ13 የሬዲዮ መገናኛዎችና 40 የእርዳታ እህል ማከማቻ መጋዘኖች ግንባታ በመከናወን ላይ ይገኛል

የኮሚሽኑንና የክልሎችን አቅም ግንባታ በ1997 በጀት ዓመት ለማጎልበት በተደረገው ጥረት ለዕለት ዕርዳታው ሥራ እገዛ የሚያደርጉ እና ግምታቸው 8.5 ሚሊዮን የሆነ 13 የሬዲዮ መገናኛዎችና 40 የዕርዳታ እህል ማከማቻ የሸራ መጋዘኖች በመገንባት ላይ ይገኛሉ:: ከንብረት አስተዳደርና ትራንስፖርት ማስተባበሪያ መምሪያ በተገኘው ሪፖርት መሠረት የመገናኛ ሬዲዮኖቹ በ650 ሺ ብር በተመደበ ዕርዳታ በአፋር 4፣ በደቡብ 3 ፣ በኦሮሚያ 3 ፣ በአማራ 2 እና በፌዴራል ደረጃ በአመዝኮ 1 ተቋቁመው ለመረጃ ልውውጥ አልግሎት ሥራ እንዲውሉ ተደርገዋል::

እንዲሁም በአፋር ፣ በትግራይ ፣ አማራ ፣ ሶማሌና በደቡብ ክልሎች በተመረጡ የዕርዳታ ማከፋፈያ ጣቢያዎች 7.9 ሚሊዮን ብር ግምት ያላቸውና እያንዳንዳቸው 350 ሜትሪክ ቶን የመያዝ አቅም ያላቸው 40 የዕርዳታ እህል ማከማቻ የሸራ መጋዘኖች የተገኙ ሲሆን፣ ከእነዚህ ውስጥ 19 ኙ ተገንብተዋል፣ የቀሪዎቹ ተከላ ሥራም በሂደት ላይ ይገኛል:: የሸራ መጋዘኖቹ የዕርዳታ እህል ጥራቱን በጠበቀ ሁኔታ በማከማቸት በአግባቡና በተፈለገው ጊዜ ለተረጂዎች ለማድረስ የሚያስችሉ መሆናቸው ታውቋል::

# በአፋርና በደቡብ ክልሎች በጎርፍ አደጋ ለተጎዱ ወገኖች 3 ሺ 700 ኩንታል በላይ የምግብ ዕርዳታ ተላከ

በአፋር ክልል በዱብቲ ወረዳ በአዋሽ ወንዝ ላይ የነበረ ድልድይ በጎርፍ በመወሰዱ እንዲሁም በደቡብ ክልል ኩራዝ ወረዳ አሞራቴ በሚባል ሥፍራ የኦሞ ወንዝ በመሙላቱ ሳቢያ ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች 3 ሺ 765 ኩንታል የምግብ ዕርዳታ ተልኳል::

በዚህም መሠረት በዱብቲ ወረዳ ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖች 2 ሺ 250 ኩንታል እህል፣ 225 ኩንታል ጥራጥሬ፣ 236 ኩንታል አልሚ ምግብ ፣ 150 ኩንታል ብስኩትና 75 ኩንታል ዘይት በድምሩ 2 ሺ 936 ኩንታል የምግብ ዕርዳታ ተጓጉዞ ዱብቲ መድረሱንና በጎርፉ ሳቢያ ተሽከርካሪ ለማይደርስባቸው ቦታዎች ከኢትዮጵያ አየር ኃይል በተገኘ ሄሊኮፕተር 350 ኩንታል የምግብ ዕርዳታ ለተጎጂዎች እንዲከፋፈል ተደርጓል:: ባለፈው ጳጉሜ 5 እና 6 ቀን 1997 ዓ.ም በተመሳሳይ በዱብቲ በጎርፍ ለተከበቡ ወገኖች በሄሊኮፕተር ከ173 ኩንታል በላይ የምግብ ዕርዳታ ተጓጉዞ መከፋፈሉም ታውቋል::

በተመሳሳይ ሁኔታ በደቡብ ክልል በደቡብ ኦሞ ዞን በኦሞ ወንዝ ሙላት ሳቢያ በኩራዝ ወረዳ በውሃ ለተከበቡ 5 ሺ ተጎጂዎች 750 ኩንታል እህልና 79 ኩንታል ዘይት ተመድቦ መጓጓዙም ታውቋል::



# ከ431 ሺ ኩንታል በላይ የምግብ ዕርዳታ ለክልሎች ተመደበ

በተለያዩ ክልሎች ለሚገኙ አስቸኳይ የምግብ ዕርዳታ ፈላጊ ወገኖች ለመስከረም ወር 1998 በጠቅላላው 431 ሺ 248 ኩንታል የምግብ እህል በአመዝኮና በመያድ የተመደበ መሆኑን ከኮሚሽኑ የዕርዳታ ኘሮግራሞች አፈፃፀምና ክትትል መምሪያ የተገኘው መረጃ ያመለክታል::

በመረጃው መሠረት ከዚሁ ለወሩ ከተመደበው ዕርዳታ ውስጥ 245 ሺ 621 ኩንታል በአመዝኮ የተመደበ ሲሆን ቀሪው 185 ሺ 627 ኩንታል ደግሞ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የተመደበው ለየክልሎቹ የሚደረገው የዕርዳታ ድልድልም በየክልሎቹ እንዳለው ችግር ስፋትና ጥልቀት እንዲሁም የተረጂዎች ብዛት አንፃር በቅደም ተከተል ሲሆን ለመስከረም ወር ከተመደበው ዕርዳታ ውስጥ ለኦሮሚያ 217 ሺ 187 ኩንታል፣ ለትግራይ 112 ሺ 110 ኩንታል፣ ለአፋር 51 ሺ 522 ኩንታል፣ ለአማራ 22 ሺ 321 ኩንታል፣ ለሶማሌ 12 ሺ 630 ኩንታል፣ ለደቡብ 9 ሺ 517 ኩንታል፣ ለድሬዳዋ 5 ሺ 960 ኩንታል የተመደበ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል::

# የላቀ አስተዋፅኦ ያበረከቱ የጥበቃ ሰራተኞች ተሸለሙ



ኮሚሽነር ሲሞን መቻለ የምስክር ወረቀትና በአጠቃላይ ብር 4ሺህ 900 ወጪ በማድረግ በጥበቃ ረገድ ጉልህ አስተዋፅኦ ላበረከቱ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን የጥበቃ ሰራተኞች ሰጡ፡፡

በመንግስት ንብረት ጥበቃ ረገድ ጉልህ አስተዋፅኦ ላበረከቱ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን የጥበቃ ሰራተኞች መስከረም 6 ቀን 1998 ዓ.ም የማበረታቻ ሽልማትና የምስክር ወረቀት ተሰጣቸው፡፡

በኮሚሽኑ የመሰብሰቢያ አዳራሽ በተካሄደው የሽልማት አሰጣጥ ሥነ-ስርዓት ላይ ለ13 የጥበቃ ሰራተኞች የምስክር ወረቀት የሰጡት ኮሚሽነር ሲሞን መቻለ ናቸው፡፡ ተሸላሚዎቹን በወጣው መስፈርት መሠረት መርጦ ለሽልማት እንዲያቀርብ ቀደም ሲል የተቋቋመው ኮሚቴ ይፋ እንዳደረገው ተሸላሚዎቹ እንደየአስተዋፅኦዋቸው በሦስት ደረጃዎች የተከፈሉ ናቸው፡፡ በዚህም መሠረት ስድስት የጥበቃ ሰራተኞች በአንደኛ ደረጃ፣ ሶስቱ በሁለተኛ ደረጃ፣ ቀሪዎቹ አራቱ ደግሞ በሦስተኛ ደረጃ ተሸላሚ ሊሆኑ እንደቻሉ ተገልጿል፡፡ ከምስክር ወረቀቱ በተጨማሪ ኮሚሽኑ በአጠቃላይ ብር 4ሺህ 900 ወጪ በማድረግ ለማበረታቻ የገንዘብ ሽልማት ያደረገላቸው ሲሆን ለአንደኛ ደረጃ ብር 5 መቶ፣ ለሁለተኛ ደረጃ ብር 3 መቶ እንዲሁም ለሦስተኛ ደረጃ የ2 መቶ 50 ብር ማበረታቻ እንደተሰጠ ለመረዳት ተችሏል፡፡

በሽልማት አሰጣጡ ሥነ-ስርዓት ላይ ኮሚሽነር ሲሞን መቻለ ባደረጉት ንግግር የሽልማቱ ዋና ዓላማ የገንዘቡ ከፍ ወይም ዝቅ ማለት ሳይሆን በዚህ ደረጃ እውቅና ማግኘት ትልቅ ነገር ነው በሚል መነሻ የተደረገ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ ኮሚሽኑ ግዙፍ ንብረት ከሚያስተዳድሩት ተቋሞች መካከል አንዱና ይህንንም በተለያዩ ቦታዎች በተበታተነ መልክ የሚገኘውን ንብረት የመጠበቁ ኃላፊነት ከባድ መሆኑን የገለጹት ኮሚሽነሩ ለሽልማት የበቁት የተወሰኑ ሠራተኞች ይሁኑ እንጂ ንብረቱን በመጠበቅ ረገድ የሁለም አስተዋጽኦ እንዳለበት አስረድተዋል፡፡ የመንግሥትን ንብረት ለመጠበቅ ሲሉ የተለያዩ ችግሮችን ለመጋፈጥ የተገደዱ የጥበቃ ሰራተኞች የመኖራቸውን ያህል በመመሳጠር በዘረፋ ላይ ተሰማርተው የነበሩ ጥቂት ግለሰቦች እንደነበሩና አስፈላጊው እርምጃ እንደተወሰደባቸው ኮሚሽነሩ አስታውሰዋል፡፡ በመጨረሻም ኮሚቴው ተሸላሚዎቹን በተገቢው መስፈርት በመምረጥና ለሽልማት በማብቃቱ ምስጋናቸውን ገልፀዋል፡፡